Amharic | አማርኛ

# Mayor's Office of Immigrant Affairs

# ለስደተኛ የኒው ዮርክ ነዋሪዎች የሚሆኑ መርጃዎች

## የኢሚግሬሽን ሁኔታዎ ምንም ይሁን ምን፣ የኒው ዮርክ ከተማ አስተዳደር እርስዎን ለመርዳት ዝግጁ ነው።

### የኢሚግሬሽን የሕግ እርዳታ

**ነፃ እና አስተማማኝ የኢሚግሬሽን የሕግ እርዳታ ለማግኘት በስልክ ቁጥር 800-354-0365**፣ ከሰኞ እስከ ዓርብ፣ ከጠዋቱ 9 ሰዓት እስከ ምሽቱ 6 ሰዓት ይደውሉ።

### የኒው ዮርክ ከተማ መታወቂያ ካርድ

**ለIDNYC ያመልክቱ**፤ ይህ እድሜያቸው 10 ዓመት እና ከዚያ በላይ ለሆኑ የኒው ዮርክ ከተማ ነዋሪዎች ሁሉ የሚሰጥ ነፃ የከተማ መታወቂያ ካርድ ነው። በኢንተርኔት አማካኝነት ያሳድሱ ወይም ለመመዝገብ ቀጠሮ ይያዙ፣ **በ 311 ይደውሉ** ወይም **nyc.gov/idnyc** ይጎብኙ።

### የእንግሊዘኛ ትምህርት

በማንኛውም ጊዜ እና ቦታ **ነፃ የእንግሊዝኛ ቋንቋ** ትምህርቶችን ይውሰዱ። ለተጨማሪ መረጃ **wespeaknyc.cityofnewyork.us** ይጎብኙ።

### የጤና እንክብካቤ

**NYC Health + Hospitals (H+H)** የድንገተኛ ጊዜ ሕክምና፣ መሰረታዊ የጤና እንክብካቤ፣ ምርመራዎች፣ ክትባቶች እና ሌሎችንም አገልግሎቶች መስጠት ይችላል። **ወደ 1-844-NYC-4NYC (1-844-692-4692) በመደወል በአቅራቢያዎ ወደሚገኝ ማዕከል መመራት ይችላሉ።**የጤና መድን ዕቅዶች ውስጥ ለመመዝገብ፣ **የNYC Care** ፕሮግራምን ጨምሮ፣ በስልክ ቁጥር **646-NYC-CARE (646-692-2273)** ይደውሉ ወይም **nyccare.nyc ይጎብኙ።**

### የአእምሮ ጤና

ለሚስጥራዊ ድጋፍ እና ከአእምሮ ጤና እንክብካቤ እንዲሁም ከሱስ መጠቀሚያ ጋር በተያያዙ ግብዓቶች ለመገናኘት በ **888-692-9355 ወይም 988** ይደውሉ፣ ወይም **"WELL" ብለው ወደ 65173 የጽሑፍ መልዕክት ይላኩ።** የኒው ዮርክ ነዋሪዎች በኒው ዮርክ ከተማ ውስጥ ስለሚገኙ የአእምሮ ጤና አገልግሎቶች በተለያዩ ቋንቋዎች የተዘጋጁ መረጃዎችን ለማግኘት **nyc.gov/mentalhealthaccess** መጎብኘት፣ ወይም የአእምሮ ጤና አገልግሎቶችን ለማግኘት የNYC 988 የኢንተርኔት ማውጫን **nyc.gov/mentalhealthservices** መጠቀም ይችላሉ።

### ለድንገተኛ አደጋዎች

**በድንገተኛ አደጋ ጊዜ በ 911 ይደውሉ።** ድንገተኛ አደጋ ማለት ከፖሊስ፣ ከእሳት አደጋ መከላከል ወይም ከአምቡላንስ አፋጣኝ እርዳታ የሚፈልግ ማንኛውም ሁኔታ ነው። **በሕግ መሠረት፣ የኒው ዮርክ ከተማ ፖሊስ መምሪያ (New York City Police Department) የወንጀል ሰለባዎችን፣ ምስክሮችን ወይም እርዳታ የሚጠይቁ ሰዎችን የኢሚግሬሽን ሁኔታ መጠየቅ አይችልም።**

### የሕዝብ ትምህርት

**እድሜያቸው ከ4 እስከ 21 የሆኑ ሁሉም የኒው ዮርክ ከተማ ልጆች በመንግሥት ትምህርት ቤት መማር ይችላሉ።** ለመመዝገብ **schools.nyc.gov/fwc** ይጎብኙ ወይም **በ 311 ይደውሉ።**

### አጠቃላይ የከተማዋ መርጃዎች እና መረጃዎች

የከተማዋን መርጃዎች ማግኘት ወይስ ችግርን ሪፖርት ማድረግ ይፈልጋሉ? በስልክ ቁጥር **311** ይደውሉ ወይም **portal.311.nyc.gov ይጎብኙ**

### የኒው ዮርክ ከተማ የስደተኞች ጉዳይ የስልክ መስመር

**በስልክ ቁጥራችን 212-788-7654** ከሰኞ እስከ ዓርብ፣ ከጠዋቱ 3 ሰዓት እስከ ምሽቱ 11 ሰዓት ይደውሉ፣ ወይም በኢሜል አድራሻችን **askmoia@cityhall.nyc.gov ያግኙን**

Amharic | አማርኛ

NYC Mayor's Office of Immigrant Affairs

# ለስደተኛ የኒው ዮርክ ነዋሪዎች የሚሆኑ መርጃዎች

## የኢሚግሬሽን ሁኔታዎ ምንም ይሁን ምን፣ መብቶች አሉዎት።

### ከኢሚግሬሽን ማጭበርበር ይጠንቀቁ

የኢሚግሬሽን የሕግ ምክር ከፈለጉ፣ ፈቃድ ካለው ጠበቃ ወይም በፍትህ ሚኒስቴር (Department of Justice, DOJ) እውቅና ከተሰጠው ተወካይ ጋር ብቻ ይነጋገሩ። እውቅና የተሰጣቸው እና የታወቁ አገልግሎት ሰጪዎችን ዝርዝር በ **nyc.gov/immigrationfraud** ማግኘት ይችላሉ።

### ከኢሚግሬሽን አስከባሪዎች ጋር በተያያዘ ያሉ መብቶች

የኒው ዮርክ ከተማ የኢሚግሬሽን ሕግ ማስከበር ሥራን አይሰራም። የፌዴራል የኢሚግሬሽን አስከባሪዎች ወደ እርስዎ ቢመጡም መብቶች አሉዎት። **nyc.gov/knowyourrights** ይጎብኙ ወይም በነፃ የኢሚግሬሽን ሕግ የስልክ መስመራችን **800-354-0365** ይደውሉ

### የሠራተኞች መብት

በኒው ዮርክ ከተማ ሕግ መሠረት የሚከፈልበት የሕመም ፈቃድ፣ አነስተኛ የደመወዝ ክፍያ፣ የትርፍ ሰዓት ክፍያ እና ሌሎችንም የማግኘት መብት አለዎት። ለመርጃዎች **nyc.gov/workers** ይጎብኙ ወይም በ **212-436-0380** ይደውሉ

### አድልዎን ሪፖርት ያድርጉ

በኒው ዮርክ ከተማ የሰብአዊ መብቶች ሕግ መሠረት ትንኮሳ እና አድልዎ ሕገ-ወጥ ናቸው። አድልዎ ሪፖርት ለማድረግ፣ እባክዎ በ **212-416-0197** ይደውሉ ወይም **nyc.gov/reportdiscrimination** ይጎብኙ

### ከቤት ውስጥ ጥቃት የመጠበቅ መብቶች

ጥቃት እያጋጠመዎት ከሆነ የኒው ዮርክ ከተማ አስተዳደር እርስዎን ለመርዳት ዝግጁ ነው። **nyc.gov/nychope** መጎብኘት ወይም የኒው ዮርክ ሲቲ የቤት ውስጥ ጥቃት የስልክ መስመርን በ **800-621-HOPE** መደወል ይችላሉ

### የተከራዮች መብት

ከቤት የማስወጣት ወይም ከአከራይዎ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች እርዳታ ይፈልጋሉ? **nyc.gov/tenantprotection** ይጎብኙ ወይም በ **311** ይደውሉ እና ነፃ የሕግ እርዳታ ለማግኘት **"tenant helpline" (የተከራይ የእገዛ መስመር)** ይበሉ

### መጠለያ የማግኘት መብት

ቤት አልባነት ካጋጠመዎት መጠለያ የመጠየቅ መብት አለዎት። የተመደበውን የቤት አልባ አገልግሎቶች መምሪያ (Department of Homeless Services, DHS) መቀበያ ማዕከል በመጎብኘት የመጠለያ አገልግሎቶችን ያግኙ። በ **311** በመደወል ተጨማሪ መረጃ ያግኙ።

### የሸማቾች ጥበቃ

የንግድ ድርጅት ጋር ማንኛውም ችግር አጋጥሞዎታል? እንደ ተጠቃሚ፣ መብቶች አሉዎት። አቤቱታዎን **nyc.gov/consumers** በመጎብኘት ወይም በ **311** በመደወል ያቅርቡ